# የመስክ ሥራዎችን በማስመልከት
# ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
# የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ዓላማ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የመስክ ተግባራዊ እንቅስቃሴውን በማስመልከት ለጋዜጠኞች ለማሳወቅ ነው፡፡

ከ97 ምርጫ በኂላ መኢአድ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች በሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመንቀሳቀስ ወስኖ ጽ/ቤቶችን ከፍቷል፡፡ ጽ/ቤቶች ባልተከፈቱባቸው አካባቢዎች ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴዎችን በማቋቋም መዋቅሩን በመዘርጋት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ባሁኑ ወቅት በብዙ ዞኖች ተከታታይ ሕዝብ የማደራጀት ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በአንዳንድ ወረዳዎች ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት ጽ/ቤቶችን ከፍቶ ከድርጅቱ አመራር እየተቀበለ የበለጠ እየተደራጀ ይገኛል፡፡ ይህንንም ለመጥቀስ ቢያስፈልግ በጋሞ ዞን የካምባ፣ የኮንሶና የደራሼ ልዩ ወረዳዎችን፣ እንዲሁም በጎፋ ልዩ ዞን ዑባ ደብረ ፀሐይና ዛላ ወረዳዎች በወላይታ ዞን በሎሶ ሶሬ፣ ቦሎሶ ቦምቤ፣ ጉኑኖ፣ ዳሞት ጋሌና ዳሞት ፉላሳ ይጠቀሳሉ፡፡ በሰሜን ወሎም ላሊበላና ዋድላ ድላንታ ኮን ላይ ጽ/ቤቶች ከፍተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ዋናው የመኢአድ ጽ/ቤትም የፓርቲያችንን እንቅስቃሴ በሁሎም ክልሎች እንዲገመግሙ ከመስከረም ወር መጨረሻ ጀምሮ አደራጅ ቡድኖችን ወደ መስክ አሰማርቶ ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት የተደራጀባቸውን አካባቢዎች እንዲያጠናክሩ ተደርጓል፡፡

በዚህ የመስክ ጉዞ አባሎቻችን ምን ተግባራት አከናወኑ? በሥራቸው ሂደት ያጋጠሟቸው ችግሮች ምንድን ናቸው? ከዚህ የመስክ እንቅስቃሴ ለወደፊቱ ሥራችን አጋዥ የሚሆን ምን ትምህርት ተቀስሟል? በጽ/ቤቶቻችንና በአባሎቻችን ላይ ገዥዎች የሚያደርሱት ጫና ምን ይመስላል? ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥበት ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ለዚህ የመስክ ሥራ አሥር ቡድኖች በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ምንም እንኳን ለቡድኖቹ የተሠጣቸው የሥራ ኃላፊነት በዞን ደረጃ የተወሰነ ቢሆንም አንዳንድ ቡድኖች በመጠኑ የወረዳዎችንም የሥራ እንቅስቃሴ ቃኝተዋል፡፡

በዚህ ሂደት ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ሁለት ቡድኖች የተንቀሳቀሱ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ቡድን ፍቼን፣ ምሥራቅ ጎጃምን፣ ምዕራብ ጎጃምን፣ አዊን፣ መተከልን፣ ደጀን ልዩ ዞንን፣ ደቡብ ጎንደርንና ሰሜን ጎንደርን ሸፍኗል፡፡ በዚሁ በሰሜን ቀጣና የተንቀሳቀሰው ሌላው የመስክ ገምጋሚ ቡድን ደግሞ ሰሜን ሸዋን፣ ከሚሴን፣ ደቡብ ወሎን፣ ሰሜን ወሎንና ትግራይን በመሸፈን ሠርቷል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያም በተመሳሳይ መልኩ በዞኖች የግምገማ ሥራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋሳ ልዩ ዞን፣ በሲዳማ፣ በጌዴኦ፣ በጉጂና በባሌ ዞኖች ተከታታይ የመስክ እንቅስቃሴተደርጓል፡፡ በተያያዘ ሁኔታ በወላይታ፣ በጋሞ፣ በደቡብ ኦሞና በዳውሮ ዞኖች ይኸው የመስክ ሥራ ተሠርቷል፡፡

በምሥራቅ ኢትዮጵያም በተመሳሳይ መልኩ የመስክ ግምገማ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሠረት በአሳይታ ዞን በዱብቲ፣ በሎጊያ፣ በአዋሽ አርባ፣ በምሥራቅ አርሲ አሰላን፣ በምዕራብ አርሲ፣ ሻሸመኔን በድሬዳዋ፣ በምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ የማጠናከርና ድርጅታዊ የአቅም ማጎልበቻ እንቅስቃሴ አድርገናል፡፡

እንዲሁም በምዕራብ ኢትዮጵያ በተደረገው የመስክ የግምገማ እንቅስቃሴ በጅማ፣ በመቱ፣ በወለጋ ነቀምቴና በአሶሳ ዞኖች የተሳካ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪም በአምቦና በወሊሶ የማደራጀት ሥራ የሚሠራ ቡድን ተሠማርቶ ተግባሩን ፈጽሞ ተመልሷል፡፡

በዚህ የመስክ ጉዞ ላይ ከመንግሥት በኩል በከፍተኛ ደረጃ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጫናዎች አጋጥመውናል፡፡

ለማስረጃም፡-

- በደቡብ ቀጣና ከተሠማሩት አደራጆቻችን መካከል አቶ በቀለ ግርማ ያለ አንዳች ምክንያት በያቤሎ ዞን ዐባያ ወረዳ ልዩ ስሙ ጓንጓ ፖሊስ ጣቢያ ለአራት ቀናት ታስረዋል፡፡
- ይህም ብቻ አልበቃም፡፡ አቶ በቀለ ያረፉበት ሆቴል ቤት ባለቤት፣ የአደራጁን መታወቂያ

በመቀማት ጉዞአቸው እንዲዘገይ አድርገውታል፡፡ መታወቂያውም የተመለሰው በማግሥቱ አቶ በቀለ አካባቢውን ለቀው ሲወጡ በአውቶቡስ ላይ ከተሳፈሩ በኂላ ነው፡፡ ይህም የሚያረጋግጥልን አንዳንድ ሆቴል ቤቶች የገዢው ፓርቲ አባላት ሀብት እንደሆኑና ሕዝቡን እንደፈለጋቸው በማፈንና በማንገላታት ሥራ ላይ ተሳትፎ እንዳላቸው ነው፡፡

- በሌላም በኩል በደቡብ ኦሞ ዞን በጂንካ ከተማ የማደራጀት ሥራ ላይ የተሠማሩትን አቶ ታዴዎስ ታንቱን የከተማው ከንቲባ ጽ/ቤት በፖሊስ አስገድዶ ለግማሽ ሰዓት ያህል በቁጥጥር ሥር አቆይቷቸዋል፡፡ ከእስር እንደተለቀቁ ከ20 ደቂቃ በኂላ የከተማው ፖሊስ አዛዥ እንደገና ጠርቷቸው የጦር መሣሪያ መያዝ አለመያዛቸውን ጠይቆ አለመያዛቸውን አረጋግጦ ለቋቸዋል፡፡
- እንዲሁም በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ ጥቅምት 18/2001 ከምሽቱ 6፡30 አደራጁ ከተኙበት ሶዶ ውበት ሆቴል በራቸውን ፖሊሶች ከበው አቶ ታዴዎስ ታንቱ የተኙበትን ቤት በማስከፈት በርካታ የፓርቲ ሠነዶችን በመ/አ ጆቢር ሶርሳ የሚመራ የፖሊስ ቡድን ዘርፏቸዋል፡፡
- በምሥራቅ ኢትዮጵያም በከፋ መልኩ በፓርቲያችን አደራጆች ላይ ተመሳሳይ አፈና ተፈጽሟል፡፡ አንዳንዶቹንም ለመጥቀስ ቢያስፈልግ በአሳይታ የፓርቲያችን የጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ዓሊሚራህ ያዬ ለበርካታ ቀናት በፖሊስ ጣቢያ እንዲታሠሩ ተደርጓል፡፡ በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ ለድርጅታችን ቤት ያከራዩትንም ግለሰብ ፖሊሶች ይዘው ለቀናት አስረዋቸዋል፡፡
- በምሥራቅ ጉጃም ደጀን ላይም የመኢአድ የሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ለሁለት ቀን ከታሠሩ በኂላ ተለቀዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመተከል የመኢአድ አመራር አባላት የሆኑት 1ኛ አቶ አዲስ ታደሰ 2ኛ አቶ ኃይለማርያም አየለ የተባሉት ከኅዳር 11/2001 ጀምሮ ይህ መግለጫ እስከተሰጠበት ሰዓት ድረስም በእስር ላይ እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

ይህን ከሕግ ውጭ የሚፈጸም የማሰርና የማንገላታት ሥራ እንዲሁም የፓርቲውን ተወካዮች በየጊዜው አላግባብ እየጠሩ የሚፈፀመው የማስፈራራት ሥራ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በእስር ላይ የሚገኙት አደራጆችና በየደረጃው የፓርቲ አስፈጻሚ አባላት ብዛት ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ከየቦታው የሚደርሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

- በአንዳንድ አካባቢዎችም የአገዛዙ ፖሊሶች በጽ/ቤቶቻችን በራፍ ላይ የተሰቀሉትን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማዎችን በማውረድና ታፔላዎችን በመንቀል ያልተቋረጠ ሕገ መንግሥቱን የጣሰ ሕገ-ወጥ ተግባር እየተፈፀመብን ይገኛል፡፡
- በገዢው ፓርቲ ባለሥልጣኖችና ካድሬዎች፣ እንዲሁም የፀጥታ ኃይሎች እየተፈፀ ያለው ሕገ ወጥ ተግባር ሕገ መንግሥቱን የሚረግጥ አሳዛኝ ድርጊት ቢሆንም በአንፃሩ ሕዝቡ ለፓርቲያችን ያለው ድጋፍና በራሱ ተነሳሽነት በማደራጀቱ ተግባር ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ በመሆኑ እንቅስቃሴያችንን የሚገታ ኃይል ሊኖር እንደማይችል ያሳያል፡፡ ይህም ሁኔታ የሕዝብ ትግል አሸናፊ መሆኑን የሚያረጋግጥልን በመሆኑ ያረካናል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ወራቶች ባካሄድናቸው የመስክ ሥራዎች በየደረጃው የሚገኙትን አባላት የመደራጀት ፍላጐታቸውን በመቀስቀስና የማደራጀት ስልቱንም በማስተማር በአጠቃላይ ግንባር ቀደም ታጋይነታቸውንና ኃላፊነታቸውን የሚወጡበት ሁኔታ እንዲመቻች ተደርጓል፡፡

እንዲሁም የፓርቲያችንን አቋም በማስመልከት ለአባላት የግንዛቤ ማጎልመሻ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የፓርቲያችንንም መዋቅር በወረዳ ደረጃ በማዋቀር ተከታታይ የማደራጀት ሥራ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በዚህም እስካሁን ድረስ በየዞኖቹ በድርጅቱ ቋሚ በጀት የሚንቀሳቀሱ ከ30 በላይ ጽ/ቤቶች የተከፈቱ ሲሆን በተጨማሪ ሌሎች ጽ/ቤቶችን ለመክፈት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የመስክ ገምጋሚዎቻችን ከአባላት ጋር ሰፊ ውይይቶች አድርገዋል፡፡ የጽ/ቤቶቻችንን አያያዝና አስተዳደር በተመለከተ በየደረጃው ለተቋቋሙ ኰሚቴዎች ትምህርታዊ መግለጫና መመሪያ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ከዚህ በፊት የነበሩ የፓርቲው ቋሚና አላቂ ንብረቶች እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ምክንያት ተዘርፈው የተወሰዱም ካሉ በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ ውይይቶች ተካሂደው የአሠራር ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

ምንም እንኳን በገዥው ፓርቲ በኩል ከፍተኛ ተፅዕኖ ቢደረግም የመስክ ገምጋሚዎቻችን ውጣ ውረዱን ተቋቁመው በዋናነት የፓርቲያችንን ድርጅታዊ ብቃት አጎልባች የሆኑ ተግባራትን አከናውነው ተመልሰዋል፡፡ በዚህም ፓርቲያችን በአሁኑ ጊዜ በሙሉ እግሩ ቆሞ በየአካበቢው የማደራጀትና ሕዝቡን የማንቃት ተከታታይ ተግባሩን ለማከናወን ከሚችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በተግባር ለማረጋገጥ በመቻላችን ከፍተኛ እርካታ ተሰምቶናል፡፡